


ኢትዮጵያና ኤርትራ ከየት ወደየት በሚል ርዕስ መጋቢት 6 ቀን፣ 2001 ዓ.ም. ሳንሆዜ፣ ካሊፎርኒያ፤ የተካሄደው ጉባኤ፣ ከተለያዩ የቤይ ኤርያ ከተሞች፤ ሳን ሆዜ፣ ሳን ፍራንሲስኮ፣ ኦክላንድ፣ ሳክራሜንቶ፣ ፍረዝኖ፣ ሞዴስቶና ሌሎች አካባቢዎች የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን የተካፈሉበት፣ በሁለቱ ህዝቦች ታሪካዊ ግንኙነትና የወደፊት ዝምድና ላይ ያተኮረ፣ ወንድማማችነትና መደማመጥ በሰፈነበት ሁኔታ የተከናወነ ታሪካዊ ውይይት ነበር።

የጉባኤው ተናጋሪዎች፣ ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድህኔ፤ ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ብሬመን፣ ጀርመኒ እና ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ፣ ከሄደርሰን ዩኒቨርሲቲ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ሲሆኑ፣ ሁለቱ ምሁራን፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ ጉዳዮች ላይ መጽሀፍትን ያበረከቱ፣ ስለሁለቱ ህዝቦች ታሪካዊ ግንኙነትና ዝምድና በአጠቃላይም በአፍሪካ ቀንድ ጉዳይ ሰፊ ጥናት ያደረጉ፣ በተለያዩ መድረኮች ሀሳባቸውን በማካፈል ተቀባይነትን ያገኙ ምሁራን ናቸው። የጉባኤው መድረክ መሪ፣ እንግዶቹን ሲያስተዋውቅ፣ የስብሰባው ተካፋዮች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

የመጀመሪያው ተናጋሪ ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን፣ እንደዚህ ባለ ስብሰባ ተገኝተው፣ በርዕሱ ላይ ሲወያዩ የመጀመሪያ ጊዜያቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ሀሳብ በማቅረብ እንዲሳተፉ ለተደረገላቸው ጥሪ አመስግነው፣ ሌላው ተናጋሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ የኢትዮጵያንና ኤርትራን እንዲሁም የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን በተመለከተ ብዙ ጥናታዊ ሥራዎች ያበረከቱ ምሁር መሆናቸውን ጠቅሰው ይህን መድረክ ከእርሳቸው ጋር በመጋራታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል። አያይዘውም፤

- ለኤርትራ ነፃነት የትጥቅ ትግል ይካሄድ በነበረበት በ1980ዎቹ፣ ጉዳዩ በፌደሬሽን መልክ እንዲፈታ በጽሁፍ ሀሳብ ገልጸው እንደነበርና፣ እሳቸው የተመኙት የሰላም መንገድ ተቀጭቶ፣ ጦርነቱ መቀጠሉን፣ ከዚያም በ1991 ዓ. ም. የደርግ ሥርዓት ወደቆ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተለይታ ሉዓላዊት ሀገር እንደሆነች አብራርተዋል። ኤርትራ በህግ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ሁኔታ የቀረበ የመፍትሄ ሀሳብ፣ ተለይታ ሉዓላዊት አገር ከሆነች በኋላ ከተከሰተ ዕውነታ ጋር ሊጣጣም አለመቻሉን በመተንተን፤ አዲስ በተከሰተው ሁኔታ ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች ሊያቀራርብ የሚያስችል የኮንፌደሬሽን ሥርዓት ነው የሚለውን አቋም መውሰዳቸውን አስረድተዋል።````````````````````````````````````````````````````````````````````````````````

- የኮንፌዴሬሽን ዝምድና በሂደት ወደተለያዩ ዘርፎች እያደገ፣ በህዝቦች መካከል መቀራረብንና መተማመንን ስለሚፈጥር በህዝቦች ፈቃደኝነት ወደ ፌደሬሽን ሊሸጋገር ይችላል። ይህ ሽግግር ሊሰምር የሚችለው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በመጠቀም መሆኑን ጠቅሰው፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የሚታወቀው ለመገንጠል አላማ ነበር፣ ነገር ግን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ አንድነትንም ለማምጣት ዋና መሳሪያ መሆኑን አስረድተው፤ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን በፈቃደኝነት የተመሰረተ ዝምድና ለመፍጠር በጋራ እንዲሰሩ ጥሪ በማድረግ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

- *በመጨረሻም፣ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በኮንፌዴሬሽንም ሆነ በፌዴሬሽን ማዛመድ የሚለው ሀሳብ ከሁለቱም ወገኖች እንቅፋቶች እንዳሉ ጠቁመዋል። በኤርትራውያን በኩል፣ ዝምድናውን የሚሰጉ፣ የሚጠራጠሩ እንዳሉ፣ አንዳንዶቹም ኢትዮጵያን እንደባላንጣ እንደሚመለከቷት፤ በኢትዮጵያውያንም በኩል ደግሞ ኤርትራውያን አንፈልግም ብለው ተለይተዋልና ከነሱ ጋር በኮንፌደሬሽንም ሆነ በፌደሬሽን መዛመድ አንፈልግም የሚሉ እንዳሉ አብራርተዋል። በማጠቃላያም፣ ከሁለቱም ወገኖች ስለሁለቱ ህዝቦች ታሪክ ፈጽሞ የተሳሳተ አመለካከት እንዳለ፣ የሀገራቱ ታሪክ ምን ያህል የተዛመደ እንደያውም በብዙ ረገድ አንድ መሆኑን የማያውቁ መኖራቸውን አስረድተው፣ እነዚህ እንቅፋቶች በአሁኑ ወቅት እየተዳከሙ መሆኑንና በሂደት ደግም ጨርሰውም ባይሆን እንደሚከስሙ እምነታቸውን ገልፀዋል።*

*ሌላው ተናጋሪ ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ፣ በንግግራቸው መግቢያ ስለ ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን አንስተው፣ ፕሮፌሰሩ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ህዝቦች የሚወዱ፣ በሁለቱ ህዝቦች ግንኙነት ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉና የወንድማማችነት ዝምድና እንዲፈጠር ብዙ ጥረት ያደርጉ ምሁር መሆናቸውን አድንቀው፣ ወደፊትም ይህን ሰፊ አላማ ግብ ለማድፍረስ በሚካሄደው ጥረት ግንባር ቀደም ሚና እንደሚጫወቱ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።*

*ፕሮፌሰር ዳንኤል፣ ከፕሮፌሰር ተስፋጽዮን ጋር በብዙ ጉዳዮች ላይ የሚስማሙ መሆናቸውን ገልፀው፣ የቀረበውን የኮንፌዴሬሽን ሀሳብ የማይቀበሉበትን ምክንያቶች ሲዘረዝሩ፣ ይህ ሥርዓት የሁለት ሀገሮች ልል ማህበር ስለሚሆን ጠንካራ ማዕላዊ መንግስት መመስረት አያስችልም። የውጭ ኃይሎችም በመካከል እየገቡ ህዝቡን ሊያጋጩ ስለሚችሉ፣ መፍትሄ እንደማይሆን አስረድተው፤ ለህዝባችን ዘላቂ ዝምድና ሊፈጥር የሚችለው የፌደሬሽን ሥርዓት እንደሆነ አብራርተዋል። የምንመሰርተው የፌዴሬሽን ሥርዓት ለኛ ብቻ ሳይሆን፣ ለአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች አዲስ ምዕራፍ ሊከፍት እንደሚችል በመዘርዘር፤*

- *የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች ወንድማማችነት፣ ሰፊ ታሪክ ያለው መሆኑን፣ ኤርትራ ውስጥ የሚኖሩ ትግርኛ ተናጋሪዎች፤ አፋሮች፣ ኩናማዎች ኢትዮጵያ ከሚኖሩ ወገኖቻቸው ጋር ሰፊ ትስስር ያላቸው መሆኑንና ያለፍላጎታቸው መለያየታቸውን አብራርተው፤ ወደፊት የሚመሰረተው ዴሞክራሲያዊ መንግስት ግን የሁለቱን ህዝቦች የጋራ ጥቅም የሚያስከብር እንደሚሆን ገልፀዋል።*

- *የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው የሚለው ሀሳብ የተሳሳተ መሆኑን ጠቅሰው፣ ብዙ ኤርትራውያን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመንግስት መዋቅር በከፍተኛ ሀላፊነት የሰሩ መሆናቸውን በመጠቆም፤ ቅኝ ገዥዎች ግን ከሚገዟቸው ህዝቦች ጋር እንዲህ ዓይነት ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑን አስረድተዋል።*

- *የውጭ ኃይሎች፣ ለራሳቸው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅም ሲሉ፣ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እንዳይሰፍን ግጭቶችን እንደሚፈጥሩ፤ በተለይም የኢትዮጵያንና የኤርትራን ዝምድና እንደማይፈልጉ፤ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እንዲኖር ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት አስፈላጊ መሆኑን፤ የኮንፌደሬሽን ሥርዓት ግን የሁለት ሀገሮች ማህበር ስለሚሆን ጥንካሬ ሊኖረው እንደማይችል፤*

- *ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች ወደ አንድነት ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ከወደብ ጥያቄ ጋር የተያያዘ አለመሆኑን፣ ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትጠቃ የኖረችው ቀይ ባህርን አቋርጠው በሚመጡ የውጭ ኃይሎች ስለሆነ፤ የሚያሳስባት የወደብ ጉዳይ ሳይሆን የሀገር ደህነት (national security) መሆኑን መረጃዎችን እየጠቀሱ አስረድተዋል። ቀጥለውም፤ የወደብን ችግር ለመፍታት ብዙ አማራጮች እንዳሏት፣ ጅቡቲ፣ ሞምባሳ፣ በርበራና ፖርት ሱዳንን ልትጠቀም እንደምትችል፤ ለምሳሌ ሲዳሞ የሚመረት ቡና በምጽዋ በኩል ተልኮ ለገበያ ከሚቀርብ ይልቅ በሞምባሳ ወይም በርበራ በኩል ቢላክ የተሻለ ትርፍ ሊያስገኝ እንደሚችል ጠቁመዋል፤*

- በመጨረሻም፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ምሁራን በቅርብ ቀን ተሰባስበው እንደሚወያዩ ገልፀው፤ የስብሰባውንም ውጤት እዚሁ መጥተው ለተሰብሳቢው ህዝብ እንደሚያቀርቡ አብስረዋል። በተጨማሪም፣ በየከተማው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያንም የጋራ ከሚቴ እያቋቋሙ እርስ በርስ መረዳዳት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ሁለቱ ምሁራን በሁለት መሪ ሀሳቦች ማለትም በኮንፌደሬሽንና ፌደሬሽን ላይ ውይይት በማካሄድ፣ መከባበር፣ መደማመጥና ማስተዋል በተሞላበት መንፈስ ሀሳባቸውን ለህዝብ በማቅረብ ያሳዩት አርአያነት ለአካባቢያችን አዲስ ምዕራፍ ሊከፍት የሚችል ነው። ከሁለቱ ምሁራን ንግግር ቀጥሎ፣ በነበረው የጥያቄና መልስ ፕሮግራም በስብሰባው ተካፋዮች ከተነሱ ጥያቄዎች፣ የቀረቡ አስተያየቶችና ግንዛቤዎች፤ ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን፤

- በኮንፌደሬሽንም ሆነ የፌደሬሽን ሥርዓት የሁለቱን ህዝቦች ለማዛመድ የሚካሄደው ጥረት ሊሳካ የሚችለው በሁለቱም ሀገሮች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲኖር በመሆኑ፤ ለውጥ ለማምጣት መተባበር እንደሚያስፈልግ፤

- ሁለቱ ምሁራን ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች ያሳዩት አክብሮት፣ ስለወደፊቱ ዝምድና ያላቸው ራዕይ ትምህርታዊ በመሆኑ፤ በሳን ሆዜ የተከፈተው መድረክ በሌሎች ከተሞችም መካሄድ እንደሚገባው፤

- ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን በአንድ አዳራሽ ተሰባሰበው ስለሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች የወደፊት እድል መወያየታቸው አዲስ ተስፋ የሚስጥ ጅምር ስለሆነ መቀጠል እንዳለበት፤

- የኢትዮጵያና የኤርትራ ምሁራን በቅርብ ተስብስበው እንደሚነጋገሩ በእንግዶቹ የተገለፀው ሀሳብ፣ የሚደገፍና ሕብረተሰባችንም የሚያበረታታ መሆኑን፣ በጉባኤው አጠቃላይ ግንዛቤ ተደርሷል።

በመጨረሻም፣ በኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን መካከል፣ በደስታ፣ ሀዘንና በጋራ ችግሮች ላይ ወንድማማች ህዝቦችን የሚያቀራርብ ከሁለቱም ወገን የተውጣጣ ስድስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቁሟል። የጉባኤውን ጠቅላላ ሂደትና የእንግዶቹን ሙሉ ንግግር በጽሁፍና በቪድዮ ተጠናቅሮ በቅርብ የሚወጣ መሆኑን እንገልፃለን።

Conference Organizing Committee
P. O. Box 1482
San Jose, CA 95109
408 646-8044
alemasmamaw@yahoo.com